# ኢትዮጵያችን

*የአንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ (አሀ! አሕ! ኢሕን) ልሳን*

**ኢትዮጵያችን ቅጽ** 1 **ቁጥር** 5 **ጥር ፳ ቀን ፪ ሺ ህ ፱ ዓ.ም.**

## <u>አይደለም እንዴ? ዋሸን እንዴ?</u>

ሰሞኑን የፈረንጆቹን አዲስ ዓመት ምክንያት በማድረግ ይመስላል ወያኔ/ኢሕአዴግ ለሀገር ውስጥ ጋዜጠኞች ጋዜጣዊ መግለጫ በጠቅላይ ሚንስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ አማካኝነት ሰጥቷል። ዶላር እስካስገኘ ድረስ ሕፃናትንና ወጣት እህቶቻችንን በቁማቸው እየቸበቸበ ያለው ወያኔ  ፀጉር መላጨት እንዳይጀምር ጠንቀቅ ነው። "አለና! ምንም አልሆንም! ምን ታመጣላችሁ! አሁንም ከማንም በላይ ነን" የሚለው የሰሞኑ የጠቅላይ ሚንስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ ጋዜጣዊ መግለጫ በሚገባ ለተረዳው ከሥልጣኑ አንፃር የወያኔን አቋምና የሀገሪቷን ቀጣይ ራዕይ መላሽ ነው።

25 ዓመት ሙሉ ሀገርና ሕዝብ ሲያተራምስ የኖረው ወያኔ ያስመዘገበው ዕድገትና ውጤት ሙስና መሆኑ የአደባባይ ምስጢር ሆኖ ሳለ ***"ሙስና በጣም ውስብስብ የሆነ ወንጀል ነው"*** በማለት ጣታቸውን ተሻሚ ሌቦቻቸው ላይ ሲያነጣጥሩ "እባብ ለእባብ ይተያያሉ ካብ ለካብ" አይሆንምን? እስቲ እንነጋገርና በጋዴ ጫማና፣ ቁምጣ ሱሪ ስኳር እየበጠበጠ የመጣው "ነፃ አውጪ" የወያኔ መንጋ ዛሬ ባለ ፋብሪካ፣ ባለ ሕንፃ፣ ሚሊየነር ሆኖ በየቢሮው ተሽከርካሪ ወንበር ላይ ሀገርና ሕዝብ እያስለቀሰ ያለው ማነው? የGolden Label (ጐልደን ሌብል) መጠጫ ብርጭቋቸው በBlack Label (ብላክ ሌብል) የሚለቀለቅላቸው "ቆንጆዬዎች" የወያኔ ባለስልጣናት አይደሉምን? በ"VIP (Very Important Person)" መዝናኛቸው ትዳራቸውንና ጎጃቸውን ረስተው ሦስት አራት ሕፃናትን በእንሰሳዊ ባህርይ እያማገጡና በገንዘባቸው እንደሸቀጥ እየገዙ ያሉት ወያኔና ባለሥልጣናቱ አይደሉምን? በተለይ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎችን ለዘመናት ከኖሩበት አካባቢና ቀዬ ያለአንዳች ጥናትና ዝግጅት እያፈናቀሉና አውላላ ሜዳ ላይ እየጣሉ በላዩ ላይ የወያኔ ባለሥልጣናት የገነቡትን ሕንጻ አንጋጦ እንዲያይ ያደረገ ቀማኛ አገዛዝ ወያኔ አይደለም እንዴ? የወያኔ/ኢሕአዴግ ሙስናዊ አገዛዝ በሀገራችን ያስመዘገበው እድገት ሥራ አጥነትን፣ ድህነትን፣ በሽታን፣ ሴሰኝነትን፣ ዝርፊያን፣ ወዘተ ለመሆኑ ከባለቤቱ ያወቀ እንዲሉ ሕዝባችን ይመስክራ። ለልጆቻቸውና ለቤተሰቦቻቸው የሀገር ቤቱ መዝናኛ ሰልችቷቸው በሕዝብና በሀገር ዶላር በዱባይ፣ በኤሺያ፣ በአውሮፓ፣ በሰሜን አሜሪካ ምርጥና ውድ ሆቴሎችና መዝናኛ ቦታዎች እየተያዘላቸው የዕረፍት ጊዜያቸውን በ "ጥቂት" ሚሊዮን ዶላር ወጪ ሚንደላቀቁት ወያኔዎችና ባለሥልጣናቱ አይደሉም እንዴ? ዋሸን እንዴ?

አይደለም እንዴ? ዋሸን እንዴ? እስቲ የኢትዮጵያ ሕዝብና ልጆቹ ይመስክሩ። የየቀን ውሸታችሁ ቀለቡ የሆነን ሕዝብ በሃሰት ሽንገላችሁ ዳግም ልታቆስሉት ባትሞክሩ ጥሩ ነው። ሕዝብና ልጆቹን እየገረፉ፣ እያሰቃዩ፣ እያስራቡ፣ እያሰሩ፣ እየገደሉ. . . "ሕዝባችን" እያሉ መጥራትና ማላገጥ በስህብናው መጫወት መሆኑን ልንገልጽ እንወዳለን። ራሱን የመከራው ገፈት ቀማሽ የሆነውን ባለቤቱን በዚህ መልኩ የሚዋሽ የሌባ ዓይነደረቅ ቢኖር ጠ/ሚ ኃ/ማርያም ደሳለኝ እና የወያኔ/ህወሀት/ኢሕአዴግ ባለሥልጣናት ናቸው። የወያኔ አገዛዝ የአሰራር ችግር ሳይሆን የሥርዓት ችግር ስለአለበት ይህ በሙስና፣ በዝርፊያ፣ በግድያ የተጨማለቀና የበሰበሰ ዘረኛ ሥርዓት በሥር ነቀል ለውጥ መወገድ እንዳለበት የሚያጠያይቅ አይደለም።

***ውድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!***

በጠ/ሚ ኃ/ማርያም ደሳለኝ አማካኝነት ሰሞኑን በወያኔ/ኢሕአዴግ የተሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ በችግርህ ላይ ዳግም ማላገጫ ነው። ራስህንና ልጆችህን መመገብ ያቃተህ የኅብረተሰብ ክፍል ላይ ዳግም የተወረወረ ዱላ ነው። በየላስቲክ ቤቱና በየጎዳናው ቀን በፀሐይ ሙቀት ሌት በብርድ ተኮራምታችሁ ምትሰቃዩት የኅብረተሰብ ክፍል ላይ እንደቅደም ተከተላችሁ የተበተነ ፍም እሳትና በረዶ ነው። በንዋይና በሥልጣን ከታወረው የህወሀት/ኢሕአዴግ አገዛዝ በምንም መልኩ ለሀገርና ለሕዝብ ቀና አመለካከት እንደማይጠበቅ የየዕለት ውጣ ውረድ ሕይወትህና ስቃይህ መስካሪ ነውና ላለመዘናጋት ቁርጠኝነትን ይጠይቃል። ለወያኔ ሰላምና መረጋጋት ማለት ሕዝብን አፍኖና ለጉሞ መጋለብ እስከቻለ ድረስ መሆኑን ከጋዜጣዊ መግለጫው መረዳት ይቻላል። ዋሸን እንዴ? አደለም እንዴ?

***"አስቸኳይ ጊዜ አዋጁ በሀገሪቷ ኢኮኖሚም ላይ ሆነ በሕዝባችን ላይ ምንም ችግር አላመጣም"*** ባዩ ጠ/ሚ ኃ/ማርያም ደሳለኝ አስረግጠው እንዳስቀመጡት ወያኔ አስተማማኝ አፈናውና ፈላጭ ቆራጭነቱ ያለአንዳች እንከን እስኪረጋገጥ በነበር እንደሚቀጥል ለፍፈዋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ታወጀ አልታወጀ በሰቆቃና በእመቃ እየተሰቃየ ከኖረ በወያኔ ዘመን ብቻ 25 ዓመት አስቆጥሯል። 25 ዓመታት የአፈና፣ የረሃብ፣ የስቃይ፣ የእሥር፣ የግርፊያ፣ የግድያ ዘመን አላረካ ያለው ወንበዴ ቡድን ግድያን ሕጋዊ ልባስ ለመስጠት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቢለፍፍ፣ ቢያቅራራ ሊያስደንቅም ሆነ ሊገርም አይገባም። **<u>የወያኔ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ተነሳ አልተነሳ ግፍና መከራው አይቀርም፣ እሥርና ግድያው አይቋረጥምና ሕዝባችን ለአዋጁ መነሳት ሳይሆን ለወያኔ/ሕወሀት/ኢሕአዴግ መነሳትና መውደም ቁርጠኝነቱን ማሳየት ይጠበቅበታል።</u>** በየቀዬውና በየአካባቢው እየተካሄደ ያለውን ፀረ-ወያኔ እንቅስቃሴ ሁሉም ኅብረተሰብ ክፍል መደገፍ ብቻ ሳይሆን የትግሉ ተሳታፊ መሆን ይጠበቅበታል። ሀገር በወያኔ ልትጠፋ ነውና የማዳን መፍትሄው በኢትዮጵያ ልጆች እጅ ነው ያለው። ተከባብሮ ለዘመናት የኖረው የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖታችን በወያኔ ምስቅልቅሉ ሊወጣ ነውና መፍትሄው ያለው ለሃይማኖታቸው ቀናኢ በሆኑት ምህመናንና የሃይማኖቶቹ መሪዎች እጅ ነው። በኢትዮጵያዊነቱ ክብርና ኩራት ያልተለየው ሕዝባችን አንድነቱ በዘረኝነት እንዲናጋና እርስ በርሱ እንዲጨራረስ የታቀደውን የወያኔን የተንኮል ድግስ ውጦት እንዲቀበር ለማድረግ አንድነታችን ወሳኝ ነው ስንል "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ (አሀ! አሕ! ኢሕን)" ድምጻችንን እናሰማለን።

***". . .በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ምክንያት አዳዲስ ነገሮች እየተሻሻሉ መጥተዋል። የመነሳቱ ጉዳይ መሠረታዊ ለውጥ ማምጣቱን መረዳት ያስፈልጋል። ሕዝቡንም ጠይቀን ሕዝቡ አስተማማኝ ሰላም አለ የሚል አስተያየት ከሰጠ. . . ሕዝባችን ሰላም፣ መልካም አስተዳደር ይፈልጋል ስለዚህ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ሙሉ በሙሉ ተሰልፏል. . .መቼ ነው የሚነሳው የሚለው ለእኛ የሚያስጨንቀን አይደለም፡፡ የሚያጣድፈን ጉዳይ የለም በኢኮኖሚያችን፣ በልማታችንና፣ በዲፕሎማሲው መስክ ያመጣው ችግር ስለሌለ አያስጨንቀንም. . ."*** እያለ በሕዝብና በሀገር ላይ ለሚያላግጥ አገዛዝ ማንነታችን አንድነታችንና ሕዝባዊነታችን ነውና

". . . ጉልበቴ በርታ በርታ

እናገኛለን የድል ዋንጫ

አሁንም አይደል ወደ ማታ . . ."

በማለት ክንድን አፈርጥሞ ለመጨረሻው ፍልሚያ መረባረብ ይጠይቃል።

ሕዝብንና ልጆቹን አፍኖ ለመግዛት "አፈናው ተስማምቶሃል ወይ?" ብሎ ሕዝብን ጠይቀን ምላሽ እንሰጣለን ብሎ ማፌዝ የሚያሳየው ወያኔ ለአፍታም ለሀገርና ሕዝብ አንዳች ደንታ እንደሌለው ነው። አምባገነንኖችና ፋሽስቶች "ሕዝባችን" እያሉ ሕዝብ መፍጀት፣ "ሀገራችን" እያሉ ሀገር ማድቀቅ ባህሪያቸው ነውና የሰሞኑ የህወሀት ጋዜጣዊ መግለጫ ለእርምትና ለመስተካከል ከማሰብ ይልቅ "ምን ታመጣላችሁ?" ንቀት መላበሱን ጀሮ ያለው አድምጧል።

መቼም በትግሉ ተስፋው የተሟጠጠው፣ አመራር መስጠት ያቃተው፣ ድርጅታዊ ሥራ ማከናወን የተሳነው ታጋይ የፖለቲካ ኃይል ቀላል አይደለምና አሁንም በደካማ ጎኑ ለመግባት የጋዜጣዊ መግለጫው ሌላው ተልዕኮ ነው።

***". . .ገዥው ፓርቲ፣ ሲቪክ ማህበራትን ጨምሮ፣ ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር ውይይት ለማድረግ አስበናል ለዚህም አደራዳሪ ተቋቁሟል፣ ኢሕአዴግን የሚወክል ኮሚቴም ተዋቅሯል. . .በመርህ ደረጃ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የተለየ የፖሊሲ አማራጭ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፤ አብዛኞቹ የራሳቸው አማራጭ ፖሊሲ የላቸውም።. . ."*** መሰል ዲስኩሮች ወያኔ በጠቅላይ ሚንስትሩ አማካይነት አስደምጦናል።

መደጋገም አይሁንብንና **<u>ከወያኔ ጋር ሰላምና ዕርቅ ከተባለ ሥልጣኑን የሚለቅበትና በሀገርና ሕዝብ ልጆች ደምና ንብረት ዝርፊያ ተጠያቂዎች ለፍርድ የሚቀርቡበት መሆን ይኖርበታል።</u>** የፈሰሰ የንጹሐን ደም የፍርድ ያለህ ይላልና፣ ቤትና ንብረታቸውን ተዘርፈው አውላላ ሜዳ ላይ የተጣሉ ቤተሰቦች እግዚኦ እያሉ ነውና፣ በጥሬ ዶላር እተቸበቸቡ ወደ ወያኔ ካዝና የገቡ የሀገር ደኖች፣ የአርሶ አደሩ መሬቶች፣ የማዕድን ክምችቶች፣ ፋብሪካዎች፣ ሆቴሎች ወዘተ ገንዘቦች ሌባው ወያኔ ለፍርድ ይቅረብልን ይላሉና፣ በጉልበትና በኃይል ያለአግባብ እየተቆረሱ የተወሰዱ አካባቢዎች ወደ ቄያችን በማለት ፍትህ ጠያቂ ናቸውና፣ የጨለማ ሕይወት ይገፉ ዘንድ የተፈረደባቸው ወጣት ሥራ አጦች፣ በየሆቴሉና ምግብ ቤቱ ደጃፍ "አድኑን/የሚበላ ያለህ" ባይ ትርፍራፊ ጉርሻ ቀላዋጮች፣ ከቆሻሻ ገንዳ ሚላስ ሚቀመስ ፈላጊዎች ለዚህ የዳረጋቸውን የወያኔ አገዛዝ የፍርዱን ቀን አሳየን እያሉ ነውና፣ በረቀቀ ተንኮል በየአረቡ ሀገር እየተሸጡ ከፎቅ የተወረወሩ፣ የታረዱ፣ የት እንዳሉ ያልታወቁ ወንድምና እህቶቻችን ጉዳይ ወያኔን ለፍርድ ያቀርበዋልና፣ የበደኖ፣ የአርባ ጉጉ፣ የጅማ፣ የኦጋዴን፣ የወልቂጤ፣ የጎንደር፣ የጎጃም፣ የአምቦ፣ ደምቢደሎ፣ የወለጋ፣ የኢሬቻ፣ የደብረብርሃን፣ የሸንኮራ፣ የመንዝ፣ የተጉለት፣ የአኝዋክ፣ የጋምቤላ፣ የደቡብ፣ የሲዳማ፣ የነገሌ፣ የቦረና፣ የሀገራችን፣ የኢትዮጵያ፣ የቄያችን፣ የብዙሃን፣ የንጹሐን፣ የግፍ ሕይወት፣ የግፍ ደም፣ የአባቶች ትካዜ፣ የእናቶች ዑ ዑ ታ፣ የሕፃናት እሪታ፣. . . ወያኔ ላይ ይጮሃል። የሀገር ያለህ! የሕዝብ ያለህ! ይላል። እግዚኦ ባዩ ሁሉም ነው። የአላህ ባዩ ተበራክቷል።

ሀገር ለበደሏና ለመከራዋ የፍትህ ያለህ ስትል ወያኔን በድርድር ስም ዕድሜውን እንዲያራዝም ለመተባበር ሳይሆን ማብቃት እንዳለበት በእርግጠኝነት ስንፋለመው ነው ፍትህና ዴሞክራሲ የሀገርና የሕዝብ ሀብት የሚሆኑት። አይደለም እንዴ? ዋሸን እንዴ?

ሀገራችን ኢትዮጵያ የግዛት አንድነቷን ጠብቃ ሁሉንም ዜጎቿን በአንድነት የምትመለከተው ወያኔን አቅፋ አይደለም። ይህ ዘመነ ጥፋት ወያኔ ሲጠፋ ሀገር ትንሣኤዋ ይሆናል። ይህ በሀገርና በሕዝብ ላይ የተከመረ ከፋፋይና ዘረኛ የወንበዴ አገዛዝ ሲወገድ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ብሎ እጅ ለእጅ ይያያዛል። ይህ ዘራፊና ቀማኛ የወያኔ አገዛዝ ሲወገድ ሕጻናት ጡጦ ያገኛሉ፣ በረሃብ የተኮራመቱ አንጀቶች ማዕድ ያገኛሉ። ይህ አምላኪ ባዕድ የወያኔ ዘመን ሲያከትም ወያኔ ያራከሰው ሃይማኖታችን ዳግም ያብባል፣ እምነታችን ኢትዮጵያችንን ይጠብቃታል። ይህ አሳዳጅ የሰው አውሬ ወያኔ ሲወገድ በስደት ዓለም ያሉ ወገኖቻችን ሀገሬ ብለው ዳግም ይሰባሰባሉ፣ የኢትዮጵያ ልጆች ያኔ እንግዳ ተቀባይነታቸውን ዳግም ያሳያሉ። ይህ የታሪክ አተላ ወደ መቃብሩ ሲወረወር ሰንደቅ ዓላማችን ከፍ ከፍ ይላል፣ ከአክሱም ጫፍ ሰንደቃችን ይውለበለባል፣ ታሪካዊ ቅርሶቻችን ያንጸባርቃሉ፣ አኩሪ ባህላችን ኢትዮጵያን ያስውባታል፣ እንጉርጉሮዬ ይዘፈንላታል። አይደለም እንዴ? ዋሸን እንዴ?

የወያኔው ጠቅላይ ሚኒስትር የአገዛዛቸው ዋና መለያና ዓርማ ስለሆነው የዘር ክልልም ዳግም አስረግጠው ተናግረዋል።

***“. . .ሕዝቡ የማንነት ጥያቄ ከአቀረበ መብቱ ነውና እናስተናግዳለን። የወሰን ጉዳይ በተመለከተ በትግራይና በአማራው ክልል መካከል ያለው ያልተፈታው የአሠራር ችግር ስላለብን ነው። ሕዝቡ ይወስናል።. . . በሶማሊያና በኦሮሚያ ክልል ያለው የወሰን ጉዳይ እንዲሁ...”***

ሀገር መበታተንን ሕጋዊ ሽፋን ለመስጠት በወያኔ የተሰነቀረው አንቀጽ 39 በማንኛውም ጊዜ ተግባራዊ እንደሚሆን እየተነገረን ነው። ወያኔ እስከ መጨረሻ እስትንፋሱ ሀገር እያተራመሰና እየዘረፈ ለመግዛት ጥረት ያደርጋል። ኃይልና ሥልጣን የሕዝብ ነውና የማይቀረው ሕዝባዊ ማዕበል ሊውጠው ከተንደረደረ የሚያልመውን “ታላቋን ትግራይ” ተግባራዊ ለማድረግ ምሥራቅ ኢትዮጵያንና “ኦሮሚያን” እንዲገነጠሉ በማመቻቸትና በአማራውና በሌላው ዘር ላይ ትርምስ በመፍጠር በ25 ዓመት አገዛዝ ዘመኑ ከኢትዮጵያ በዘረፈው ሀብትና ንብረት እንዲሁም ከየትኛውም ክልል በተለየ መልኩ በክልሉ በገነባቸው ተቋማትና ወታደራዊ ሽፋን አማካኝነት “ታላቋን ትግራይ” ተግባራዊ ለማድረግ ሲጠነሰስ የነበረው ዕቅዱ የመጨረሻዬ ይሆናል የሚል ቅዠቱ ዛሬ አብሮት እንዳለ ይስተዋላል። ለዚህም ቅድም ዝግጅት ይረዳ ዘንድ ነው ወልቃይትን ወደ ትግራይ ክልል ያስገባው። የዚህ ድብቅ የወያኔ ተልዕኮ “እኛ ካልገዛናት ኢትዮጵያን እንበትናለን” የሚለው ምኞታዊ ተስፋ ባይሳካም ሀገር ለማጥፋትና ለማዳከም የሚያበረክተው አስተዋጽዖ ቀላል አይሆንምና የሁሉንም ዘሮች ኢትዮጵያዊ አንድነትና ብሔራዊ ስሜት ማበብን ይጠይቃል። የተበታተነች ኢትዮጵያን ላለማየት በተባበረ ክንድ ወያኔን ማውደም ይጠይቃል። በሕዝብ አንድነት ላይ የተመሠረተች ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለማየት ኢትዮጵያ ሀገሬ ብሎ መነሳትን ይጠይቃል። በዘር መከፋፈል ለወያኔ ወጥመድ በመመቻቸት ለሀገር መዳከምና መበታተን ዕድሉን ያሰፋልና ኢትዮጵያዊነትን ተሸክመን ታሪክ መስራት ይኖርብናል።

የአሉላ አባ ነጋ ዶጋሌ ኢትዮጵያ ነች፣ የዓፄ ዮሐንስ መተማ ኢትዮጵያ ነች፣ የዓፄ ቴዎድሮስ መቅደላ ኢትዮጵያ ነች፣ የዓፄ ምንሊክ ዐድዋ ኢትዮጵያ ነች፣ የጀግኖች አርበኞቻችን ማይጨው ኢትዮጵያ ነች፣ የጦና ወላይታ ኢትዮጵያ ነች፣ የአቡነ ጴጥሮስ እምነት ኢትዮጵያ ነች፣ የሁላችን ሀገር ኢትዮጵያ ነች። ይህን ያልን ጊዜ ኢትዮጵያችን ዳግም ታብባለች፣ ለሀገርና ለሕዝብ የፈሰሱ ደሞች፣ የተከሰከሱ አጥንቶች የታሪክ ቦታቸውን አገኙ። ያዙ። አይደለም እንዴ? ዋሸን እንዴ? ኢትዮጵያችን ለዘለዓለም ትኑር።

***ውድ የኢትዮጵያ ወጣቶችና ተማሪዎች ሆይ!***

በኢትዮጵያ የትግል ታሪክ ወጣቶችና ተማሪዎች ጉልህ ሚና ተጫውተዋል አሁንም ይጫወታሉ። የኅብረተሰቡ አካል የሆኑት ተማሪዎችና ወጣቶች ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው መብትና ነፃነት ግምባር ቀደም በመሆን ታግለዋል፣ መስዋዕትነት ከፍለዋል። ወያኔ ሀገሪቷን ከተቆጣጠረ ጊዜ ጀምሮ ወጣቶች ሀገራቸው ኢትዮጵያን እንዳይመለከቱ በተለያየ መልኩ እየተከታተለ ሲኮረኩማቸው ኖሯል። ወጣቶች በአልባሌ ሱስ በመጠመድ ሀገር እንዳይመለከቱ ተጥሯል። ወጣቶች ሀገራቸውን ጠልተው ስደት ናፋቂና ባዕድ አምላኪ ይሆኑ ዘንድ ወያኔ ሌት ተቀን ሠርቷል። ወጣቶች ከሀገራቸው ይልቅ የግል ፍላጎታቸውን እንዲያሳድዱ ተዘምቶባቸዋል። ወጣቶች ከሆዳቸው ሌላ እንዳያስቡ በረሃብ አለንጋ ተገርፈዋል። ወጣቶች ለወያኔ አገዛዝ እንዲሰለሉ አንድ ለአምስት ተጠርንፈዋል። ወዘተ....ወዘተ. ግና ይህ ሁሉ ሆኖ በወያኔም አገዛዝ ወጣቶች ከሕዝብና ሀገራቸው ጎን በመሆን ከፍተኛውን የተጋድሎ ድርሻ ተወጥተዋል እየተወጡም ይገኛሉ። በተለያየ ወቅት ያስመዘገቡት ተጋድሎና የከፈሉት መስዋዕትነት ታሪክ አይረሳውም።

የጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋዜጣዊ መግለጫ ወጣቱ ላይ ማነጣጠር እንዳለባቸው ጠቆም አድርጎ አልፏል። አዎ ወያኔ ምን ያህል የወጣቶችን አልገዛምና አሻፈረኝ ባይነትን ተገንዝበዋልና እንዴት አድርገው በመዳፋቸው ሥር እንደሚያስገቧቸው ዋነኛው ዕቅዳቸው መሆኑን ነግረውናል። በቅርቡ በአማራውና በኦሮሞ ልጆች አካባቢ ቀደም ሲልም በእስላምና እምነት ተከታዮች የ“ድምጻችን ይሰማ” እንቅስቃሴ ወቅት ከፍተኛውን ድርሻ የተጫወቱት ወጣቶች በመሆናቸው ከወያኔ ዕድሜ አንፃር መሸመድመድ ይኖርባቸዋል። ለወያኔ አንድ ለአምስት ጥርነፋ ሳይበገር ለጥይትና ለእሥር የተዳረገውን ወጣት ቤቱ ይቁጠረውና ለቀጣይ የወያኔ ዕድሜ ማራዘሚያ ስልት ወጣቱ

እንዴት መሸመድመድ እንዳለበት ***“ወጣቶቻችን የባይተዋርነት፣ የመገለል ስሜት እንዳላቸው ተረድተናል”*** በሚል ውስጠ መርዝ ወያኔያዊ ተንኮል ከተጀመረው ሕዝባዊ ንቅናቄና ፍልሚያ ወጣቱን ለማግለልና ለማሰናከል ለታቀደው ዕቅድ ነቅታችሁ መከላከል እንደሚገባ ለማሳሰብ እንወዳለን።

ከእንግዲህ ከወያኔ ጉያ መወሸቅ ከእሥርና ግድያ አያድንምና መፍትሄው ትግል ነው። ድመት አይጥን ይዛ ከመብላቷ በፊት ያለውን ጨዋታ ወያኔ በወጣቶችና ተማሪዎች ላይ ዳግም ሊተገብረው መሆኑን ተረድታችሁ በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ ትግሉን አፋፍሙት፣ ሀገራችሁንና ሕዝባችሁን ከጥፋት አድኑ። ከእንግዲህ ከወያኔ ጋር ጨዋታ “አይጥ ለሞቷ የድመት አፍንጫ ታሸታለች” ነውና እጅ እንዳትሰጡ። ለሀገርና ሕዝብ አውዳሚው ወያኔ እጅ መስጠት ሳይሆን እጃችሁን አሳዩት፣ ግንባርህን አሳየው። አይደለም እንዴ? ዋሸን እንዴ?

በመጨረሻም “አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ (አሀ! አሕ! ኢሕን)” ሀገራችንንና ሕዝባችንን ከወያኔ መዳፍ ሥር ነፃ በማውጣት ያልተሸራረፈ የዜግነትና ሰብአዊ መብት የተከበረባት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ ፀረ-ወያኔ ትግሉን ማፋፋም ዋነኛው አማራጭ በመሆኑ ለጠላት ሳይጋለጡ ለመሰባሰብና ለመደራጀት ለሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች ሕዝባዊ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

በሌላ በኩል በወያኔ/ህወሀት/ኢሕአዴግ አካባቢ የተኮለኮላችሁ የጥቅምና የፖለቲካው ተጋሪዎች ከሕዝብ ፍርድ ልታመልጡ የምትችሉት ከወያኔ ውድቀት በፊት ድምጻችሁን አሰምታችሁ ሰልፋችሁን ከሀገርና ከሕዝብ ጎን በማድረግ በመሆኑ “ካልተሳፈሩበት ቶሎ ተሽቀዳድሞ ጊዜ ታክሲ አይደለም አይጠብቅም ቁሞ” እንዳሉት ፀሐፊ ጊዜ ሳይቀድማችሁ ሰልፋችሁን ታሳምሩ ዘንድ የቅርብ ጊዜ ታሪክን ዞር ብላችሁ ተመልከቱ እንላለን።

**ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!**

**እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!**

**“አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ”**

ጥር 05 ቀን 2009 ዓ.ም. (January 13, 2017)

**ማሳሰቢያ ፡**

- ውድ ወገኖቻችን ይህንን «አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ» «***ኢትዮጵያችን***» ልሳን በተለይ በሀገር ቤት ኮምፒዩተር የማግኘት ዕድል ለሌላቸው በማባዛት ታሰራጩት ዘንድ ቀና ትብብራችሁን በትህትና እንጠይቃለን።
- «አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ» መስከረም 8 ቀን 2009 ዓ.ም. እራሱን ይፋ ያደረገ ሕዝባዊ ድርጅት ሲሆን የንቅናቄውን ማንፌስቶና ፕሮግራም www.ethiopiachen.org ከሚለው ድረ ገጻችን ማግኘት ትችላላችሁ።

ኢሜል ፡ ethiopiachen2009@gmail.com
info@ethiopiachen.org

ድረ ገጽ ፡ www.ethiopiachen.org
www.ethiopiachen.com

ምስለ ገጽ : Ethiopiachen Hagerachen